የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

# የስብሰባ ጥሪ

የተከበራችሁ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሆይ!

ዛሬ ሀገራችን ና ህዝባችን የሚገኙበት ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ፣ አስጨናቂና አደገኛ መሆኑ፤ በግልፅ የታወቀና ማንኛችንም የምንገነዘበው ነው። በዚህ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶችና ያገባናል የሚሉ ወገኖች ሁሉ የበኩላቸውን ትንተናና መፍተሄዎች ለማቅረብ እየሞከሩ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲም፣ (ኢህአፓም) በበኩሉ በዚህ ታላቅና አንገብጋቢ በሆነ የሀገራችን ጉዳይ ላይ ያለውን አቋምና ራዕዩን፣ የድርጅቱን እንቅስቃሴና የትግሉን ሁኔታ፤ ለህዝብ ለማሳወቅና ለመወያየት ዝግጅት አድርጓል። በዚህ ዝግጅት ላይም፤ ከድርጅቱ አህጉራዊ አመራር በተጨማሪ፣ በአውስትራሊያ ከሚገኙም የተለያዩ ስቴቶች የሚመጡና የሚሳተፉ እንግዶች ይኖሩናል።

ስለሆነም፣ ለዚህ የሀገር ጉዳይ፣ ድርጅቶችና ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሃላፊነት ስላለበት፣ በስብሰባው ተገኝታችሁ የበኩላችሁን አስተዋፅዖ ታበረክቱ ዘንድ፣ በሜልበርን ከተማና በአካባቢው ለምትገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ጥሪያችንን በአክብሮትና በትህትና እናቀርባለን።

ከምስጋና ጋር

የሜልበርንና አካባቢው ኢህአፓ ኮሚቴ

ቀን (Date):ነሐሴ ፳፱ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም (Sept 4 / 2011)

ቦታ (Address): YMCA Corner of Market St and Essex St
Footscray, Vic, 3011

ሰዓት (Time): **1:00 – 6:00 PM**